Baankii Hojii Gamtaa Oromiyaa
የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ
Bank of Oromia

**ለኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች**

**የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ**

የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ. 17ኛ የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 366 (1)፣ 367 (1)፣ 370 እና 371 (1) እንዲሁም የባንኩ መመሥረቻ ፅሑፍ አካል በሆነው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6 (1) (4) መሠረት ታህሳስ 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በአዳማ ከተማ፣ ገልማ አባ ገዳ ይካሄዳል፡፡ ስለሆነም ባለአክሲዮኖች በተጠቀሰው ቦታ፣ ቀንና ሰዓት ተገኝታችሁ የጉባኤው ተሳታፊ እንድትሆኑ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ይጋብዛል፡፡

**የጉባኤው አጀንዳዎች**

1. የጉባኤውን ድምፅ ቆጣሪዎች መሰየም/መምረጥ፣
2. ምልዓተ-ጉባኤው መሟላቱን ማረጋገጥ፤
3. የጉባዔውን አጀንዳዎች ማጽደቅ፣
4. እስከ ጉባዔው ድረስ የተደረጉትን የአክሲዮኖች ዝውውሮች እና የባለአክሲዮኖችን ብዛት ማሳወቅ፣
5. እ.ኤ.አ. የ2020/21 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ፣
6. እ.ኤ.አ. የ2020/21 የባንኩን የውጭ ኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ፣
7. በዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ ወርሃዊ አበልና ዓመታዊ ክፍያን መወሰን፣
9. እ.ኤ.አ. ለ2021/22 የውጭ ኦዲተሮችን መሾም እና ክፍያቸውን መወሰን፣
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ማካሄድ፣
11. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ፣

**ማሳሰቢያ፡**

1. የኮሮና (ኮቪድ-19) ወረርሽኝን ለመከላከል መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት የስብሰባው አዳራሽ መያዝ በሚገባው ተሰብሳቢ መጠን ላይ ገደብ በመጣሉ ጉባኤው ቁጥራቸው በተወሰኑ ተሳታፊዎች የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ባለአክሲዮኖች ወኪል በመሾም በጉባኤው ላይ እንዲሳተፉ ቦርዱ እያበረታታ፣የጉባኤዉ ተሳታፊዎች በመመሪያዉ መሰረት ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያስችሉ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ያለባቸው መሆኑን፣
2. ባለአክሲዮኖችም ሆኑ ተወካዮች በጉባኤው ለመሳተፍ ሲመጡ የራሳቸውንም ሆነ የወካያቸውን የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ መያዝ ያለባቸው መሆኑን፣

3. በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕጉ አንቀፅ 377 (1) መሠረት አዲስ አበባ፣ፍላሚንጎ አካባቢ ጌት ሃውስ ህንፃ ላይ በሚገኘው የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም በአቅራቢያቸው በሚገኘው የባንኩ ቅርንጫፍ በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የውክልና መስጫ ቅጽ በመሙላት በተወካያቸው ተገኝተው ድምፅ እንዲሰጡ ማድረግ የሚችሉ መሆኑን፣
4. ድርጅትን (የኅብረት ሥራ ማኅበርን ወይም ሌላ ድርጅትን) ወክሎ የሚቀርብ ተወካይ የድርጅቱ/የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዞ መቅረብ ያለበት መሆኑ፤አለዚያም በባንኩ የውክልና መስጫ ቅጽ መሠረት ውክልና የተሰጠው መሆኑን፣
5. ከላይ በተራ ቁጥር 2 እና 3 ሥር ከተመለከቱት ውጭ በውክልና በስብሰባው ላይ ለመገኘት የሚፈልጉ ካሉ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል የተሰጠ በጉባኤው ለመሳተፍ እና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን፣
6. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ባስመዘገበው ተንቀሳቃሽ/ሞባይል ስልክ ቁጥር የባለአክሲዮኑ መለያ ቁጥር የሚላክ በመሆኑ፡ ባለአክሲዮኖች/ተወካዮች ይህንኑ መለያ ቁጥር በጉባኤዉ ዕለት ይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን፣
7. ተወካዮች ወደ ጉባኤው ሲመጡ ወካዩ ባለአክሲዮን ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው/ያላት ወይም ትውልደ-ኢትዮጵያዊ መሆኑን/መሆኗን የሚያረጋግጥ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፈቃድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ ይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

**<u>አድራሻ፡</u>**

አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ቀበሌ 17፣ ፍላሚንጎ አከባቢ፤ ጌት ሐውስ ህንፃ፣ ከ1-6ኛ ፎቅ፣

ስልክ፣ (251) 11 515 02 29 ፋክስ (251) 11 515 04 89፣ ፖ.ሣ.ቁ.፣ 16936፣

ኢሜል፡ coopbank@ethionet.et.

ድረ ገፅ፡www.coopbankoromia.com.et

ዋና የንግድ ምዝገባ፡ KK/AA/3/0001918/2004; የባንክ ሥራ ፈቃድ፡-LLB/008/2004;

ይህ ማስታወቂያ እስከተዘጋጀበት ቀን ድረስ የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 6,330,880,800.00.

**የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ.**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**